


**አቶ አስማማው አሰፋ ጥሩነህ**

**(1948 - 2002)**

**(1956 - 2010)**

# የአቶ አስማማው አሰፋ ጥሩነህ አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ አስማማው አሰፋ ጥሩነህ ከእናቱ ከወ/ሮ ባንችዋል ዓለሙና ከአባቱ ከአቶ አሰፋ ጥሩነህ በጎጃም ክፍለ ሀገር በባህር ዳር አውራጃ በአዴት ወረዳ የካቲት 8 ቀን 1948 ዓ.ም. (February 15 1956) ተወለደ። ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በአዴት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትሏል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመጀመሪያ በባህር ዳር ከተማ ቀድሞ አፄ ሠርፀ ድንግል አሁን ጣና ሀይቅ በሚባለው ትምህርት ቤት ቀጥሎም አዲስ አበባ በሚገኘው በሽመልስ ሀብቴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብቶ አጠናቅቋል።

በ1967 ዓ.ም. በከፋ ክፍለ ሀገር በጊሚራ አውራጃ በእድገት በሕብረት ዘመቻ የተሳተፈ ሲሆን እዚያ በነበረበት ወቅት ሕዝብን በማስተማርና የሕዝብን ኑሮ ሊለውጡና ሕዝብን ሊጠቅሙ በሚችሉ ተግባራዊ ስራዎች ላይ በመሳተፍ ወገኖቹን በቅንነት ሲያገለግል ቆይቷል። ወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመሰረታዊ ለውጥ የተነሳሳበትና ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ወቅት ስለነበር አቶ አስማማው የዚሁ የለውጥ እንቅስቃሴ ተሳታፊ ነበር። የሕዝብ መከራና ስቃይ ከልብ የሚሰማው፤ ለወገን ደህንነትና ብልጽግና ራሱን አሳልፎ ለመስጠት ወደ ኋላ የማይል ቁርጥ የኢትዮጵያ ልጅ ስለነበር በእድገት በሕብረት ዘመቻ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ሊግን (ኢሕአወሊ) በመቀላቀልና ቀጥሎም የኢሕአፓ አባል በመሆን ለሰላም ለዴሞክራሲና ለሕዝብ ሙብት መረጋገጥ በተደረገው ትግል ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ጉልህ ተሳትፎ ሲያደርግ ቆይቷል።

የኢሕአፓ አባል ከሆነ ጀምሮ ሕዝብን በማደራጀት ና ትግሉ በማጠናከር በኩል አቶ አስማማው ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ሲሆን ለትግሉ በራሱም ኑሮ ሆነ በቤተሰቡ ህይወት ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሏል። በትግል ውስጥ በነበራቸው ተሳትፎ ምክንያት አቶ አስማማውንና ወንድሙን የደርግ መንግስት ለመግደል ይፈልጋቸው ስለነበር ከቤት በመሰወራቸው ወላጅ አባታቸው አቶ አሰፋ ጥሩነህ በልጆቹ መጥፋት ተወንጅለው በአረመኔው መንግሥት በግፍ ተረሽነዋል። አቶ አስማማውም በቅርብ ሲደረግ ከነበረው የደርግ አፈናና ክትትል ለበርካታ ጊዜያት ማምለጥ ቢችልም የቀይ ሽብር ግድያው በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋቱና አደጋውም እየከፋ በመምጣቱ ሳይወድ በግድ የሚወዳትን አገሩን ትቶ ወደ ሱዳን ለመሰደድ ተገድዷል። በ1973 (በ 1983) ወደ አሜሪካ መጥቶ ኑሮ ቢመሰርትም ከኢሕአፓ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለሕዝብ በሚደርገው ትግል በግንባር ቀምትነት ተሳትፎ ሲያደርግ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ ቆይቷል።

በአሜሪካና አገር ሲያትል በሚገኘው Central Community College በአካውንትንግ የ ኤ.ኤ ዲግሪውን የተቀበለ ከመሆኑ በላይ በተላያዩ መስሪያ ቤቶች ሰርቷል።

አቶ አስማማው ትሁት፤ ሐቀኛና ስው አፍቃሪ፤ ለተቸገረ ደራሽ፤ ከራሱ የበለጠ የሰው ችግር የሚሰማው፤ የሀገርና የወገን ፍቅር የሚያንገበግበው ዜጋ ስለነበር በትግል አጋሮቹ፤ በጓደኞቹና፤ በወዳጆቹ እንዲሁም

በሲያትል ከተማ ነዋሪ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ታዋቂና ተወዳጅ ነበር። በሲያትል ከተማ በተደረጉ ማህበረሰባዊና ፓለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁሉ አቶ አስማማው ግንባር ቀደም ተሳታፊ የነበረ ከመሆኑም  በላይ እስከዕለተ ሞቱ ድረስ ማህበረሰቡን በቅንነት ሲያገለግል ቆይቷል።

አቶ አስማማው ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ባደረበት ሕመም ምክንያት በህክምና ሲረዳ  ቆይቶ ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. በተወለደ በ54 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። በአጭር ጊዜ ህመም በአፍላ እድሜው ሳይታሰብ በሞት በመለየቱ ለቤተ ሰቡና ለወዳጆቹ ሁሉ የማይረሳ ስቀቀን ሆኗል። አቶ አስማማው አሰፋ ጥሩነህ በህወይወት ዘመኑ ትዳር ይዞ ሶስት ሴቶች ልጆች አፍርቷል። የመጀመሪያ ልጁ ሳምራዊት በስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ስትሆን ማህሌትና ሊዲያ ለጋ ወጣቶች ናቸው። ባለቤቱ ወ/ሮ የኋላሸት ጅማ በህይወት ዘመኑ ከጎኑ በመቆም የአላማው ደጋፊና ተባባሪ ሆና የቆየች ከመሆኗ ሌላ ታሞ በነበረበት ወቅት ከፍተኛ ትብብርና ድጋፍ በመስጠት አስታመዋለች።

አቶ አስማማው  ገና  በአፍላው ዘመኑ በድንገት በሞት ቢለየንም በደግነቱ፤ በቅንነቱና  በመልካም ስራው እንዲሁም በአይበገሬ የሕዝብ ልጅነቱ ምን ጊዜም ስናስታውሰው እንኖራለን።

ታሞ በነበረበት ወቅት በተለያዩ መንገዶች ለጠየቁት፤ ላበረታቱትና የተላያዩ ርዳታና ትብብር ላደረጉለት ወዳጆችና ወገኖች ሁሉ በህይወት እያለ ምስጋናው እንዲተላለፍለት አጥብቆ የጠየቀ በመሆኑ በዚህ አጋጣሚ  ምስጋናውን  እናስተላልፋለን።

## A Short Biography of *Ato* Asmamaw Assefa Truneh

Ato Asmamaw, the son of *Weyzero* (Mrs.) Banchiwal Alemu and *Ato* (Mr.) Assefa Tiruneh, was born in Adet, Gojjam province, western Ethiopia, on February 15, 1956.

Asmamaw attended primary school in Adet; and secondary education at Atse Serse Dingle (the now Tana Haiq) in Bahir Dar and at Shimles Habte in Bahir Dar and Addis Ababa.

During the 1975 nation-wide illiteracy campaign, otherwise known as Progress through Co-operation Campaign, Asmamaw was assigned in Gimera Awraja, Keffa Province, Southern Ethiopia. While there, in addition to teaching, Asmamaw actively participated in mobilizing and organizing the peasantry against the remnants of the Haile Sellassie's regime. It was his strong belief in justice, equality and fairness that convinced him to join the youth wing of one of the radical political movements in Ethiopia, Ethiopian People Revolutionary Party.

Asmamaw's active involvement in the struggle against the military junta, also known as the *Derg*, which usurped political power in 1974, brought the wrath of the junta against him and his family. Asmamaw and his younger brother were targeted for assassination by the military junta. As the military government intensified the Red Terror and the extra-judicial killing to stifle the popular uprising in Ethiopia, Asmamaw and his brother left their country for Sudan. Unable to find Asmamaw and his younger brother, the junta accused their father of aiding counter-revolutionaries, his sons! The junta executed *Ato* Assefa without the due process of the law.

So much was Asmamaw's belief in the success of the struggle for freedom and so much was his desire to see Ethiopia progress, and so much was his conviction that one day Ethiopians will enjoy democratic rights, Asmamaw continued his struggle in Sudan as well as the United States--until his last breath.

Due to health problem, Asmamaw had been admitted into hospital. While he withstood the junta, Asmamaw, however, was unable to recover from his illness. He died on Thursday, June 3, 2010. *Ato* Asmamaw is survived by his daughters, Samirawit, who is attending Stanford University, Mahlet, Lydia and his beloved wife, *Weyzero* Yehualashet Jimma, who never left his side until the end.

Although Asmamaw left us, he will be remembered for his kindness, honesty, determination and his fight for the greater good. He will be greatly missed.